# ከእግዚአብሔር ጋር የጠለቀ ግንኙነት ማድረግ
## ክፍል ፩

በዘመናት መካከል አማኞች እግዚአብሔርን ለማምለክ ብለውም እምነታቸውን ለመግለፅ የተለያዩ መዝሙሮችን ፅፈዋል። አንዳንዶቹ ለአጭር ጊዜ የታወቁ ሆነው ከዚያም ሲጠፉ፣ ሌሎቹ ደግሞ ረዥም ዘመን አልፈው ከመምጥታቸውም ባሻግር በተለያዩ ቋንቋዎችም ተተርጉመው ይዘመራሉ። ታዲያ በመዝሙረ ዳዊት ላይ ተፅፈው የሚገኙት 150 የተውጣጡ መዝሙሮች በየትኛው ዘመን ከተፃፉት መዝሙሮች ይልቅ ብዙ ዘመናትን አልፈው የመጡና ልዩ የሆነ ይዘት ያላቸው እንደሆኑ መረዳት አያዳግትም። እነዚህ መዝሙሮች በሺህ የሚቆጠሩ አመታትን ያስቆጠሩ ቢሆኑም፣ አሁን ባለንበት ዘመን የሚዘመሩት ብዙ መዝሙሮች መልእክቶቻቸው ከዚሁ ከመዝሙረ ዳዊት የተወሰዱ ናቸው። በውስጣቸውም ደስታና ሃዘን፣ በእግዚአብሔር ላይ ያለ እምነት እንዲሁም የልብ ሃዘንና ለቅሶ፣ እይተፈራረቁ የተፃፉበት ሲሆን፣ በየትኛውም ርእስ ላይ ቢፃፉ እነዚህ መዝሙሮች አማኝ በእግዚአብሔር እንዲታመን፣ እርሱንም በመታዘዝ መንገድ እንዲሄድና ከልብ የሆነ አምልኮ ለአምላኩ እንዲያቀርብ በማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረው የሚያደርጉ ጥልቅ የሆነ መልእክት ያላቸው መዝሙሮች ናቸው። በሚቀጥሉት ተከታታይ ክፍሎች አለፍ አለፍ በማለት እነዚህ መዝሙሮች በውስጣቸው ያዘሉትን መልእክቶች እንመለከታለን።

መዝሙረኛው እንደዚህ ይላል፡-

“ምድር ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር እልል በሉ፥

በደስታም ለእግዚአብሔር ተገዙ፥ በሐሤትም ወደ ፊቱ ግቡ።

እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደ ሆነ እወቁ እርሱ ሠራን እኛም አይደለንም እኛስ ሕዝቡ የማሰማርያውም በጎች ነን።

ወደ ደጆቹ በመገዛት፥ ወደ አደባባዮቹም በምስጋና ግቡ አመስግኑት፥ ስሙንም ባርኩ

ወደ ደጆቹ በመገዛት፥ ወደ አደባባዮቹም በምስጋና ግቡ አመስግኑት፥ ስሙንም ባርኩ”

(መዝ. 100)